# የሐዋርያው ፡ የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡
# ወደ ፡ ሮሜ ፡ ሰዎች ።

## ምዕራፍ ፩ ።

ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳው ፩፤፪፤
ሎስ በነቢያቱ አፍ በቅዱሳን መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋ
ለሰጠው ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ ። ይህም ወንጌል ፫፤፬፤
በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለ ተወለደ እንደ ቅድስና መንፈስ
ግን ከሙታን መነሣት የተነሣ በኃይል የእግዚአብሔር
ልጅ ሆኖ ስለ ተገለጠ ስለ ልጁ ነው ፤ እርሱም ጌታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። በእርሱም ስለ ስሙ በአሕዛብ ፭፤
ሁሉ መካከል ከእምነት የሚነሣ መታዘዝ እንዲገኝ ጸጋ
ንና ሐዋርያነትን ተቀበልን ፤ በእነርሱም መካከል የኢየ ፮፤
ሱስ ክርስቶስ ልትሆኑ የተጠራችሁ እናንተ ደግሞ ናችሁ ።
በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን ልትሆኑ ለተጠ ፯፤
ራችሁ በሮሜ ላላችሁት ሁሉ ፡ ከእግዚአብሔር ከአባታ
ችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ
ይሁን ።

እምነታችሁ በዓለም ሁሉ ስለ ተሰማች አስቀድሜ ስለ ፰፤
ሁላችሁ አምላኬን በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ ።
በልጁ ወንጌል በመንፈሴ የማገለግለው እግዚአብሔር ፱፤፲፤
ምስክሬ ነውና ፤ ምናልባት ብዙ ቆይቼ ወደ እናንተ አሁን
እንድመጣ በእግዚአብሔር ፈቃድ መንገዴን እንዲያቀና
ልኝ እየለመንሁ ሁልጊዜ በጸልዬ ስለ እናንተ ሳላቋርጥ
አሳስባለሁ ። ትጸኑ ዘንድ መንፈሳዊ ስጦታ እንዳካፍላ ፲፩፤
ችሁ ላያችሁ እናፍቃለሁና ፤ ይህንም ማለቴ በመካከላ ፲፪፤
ችን ባለች በእናንተና በእኔ እምነት አብረን በእናንተ እን
ድንጽናና ነው ። ወንድሞች ሆይ ፡ በሌሎቹ አሕዛብ ደግሞ ፲፫፤
እንደ ሆነ በእናንተም ፍሬ አገኝ ዘንድ ብዙ ጊዜ ወደ እና
ንተ ልመጣ እንዳሰብሁ እስከ አሁን ግን እንደ ተከለከ
ልሁ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ ። ለግሪክ ሰዎችና ላልተማ ፲፬፤

